
## የተሻሻለ የወተት ከብቶች

# አያያዝ መመርያ

## የወተት ከብት እርባታ ስራ

## አመራር መመሪያ

2010 ዓ.ም




Designed & Printed by
master print
አራት ኪሎ ፡፡ +251 111 557 788 ገርጂ ፡፡ +251 116 298 777
31362 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
www.masterprintaddis.com

# 5. የወተት ከብት  እርባታ ስራ አመራር መመሪያ

የወተት ከብት እርባታ እንደ ማንኛውም ለትርፍ የተቋቋመ የንግድ ሥራ አትራፊ ይሆን ዘንድ የመረጃ ስርዓትና የንግድ ስራ አመራር ወሳኝ ሚና አላቸው። ከእንሰሶች ምርት ጀምሮ ባጠቃላይ ከእርባታው ጋር ተያይዞ ያሉ ወጭዎችና ገቢዎች በሚገባ ከተያዙ የእርባታውን ትርፋማነት በሚገባ ለመረዳት ያስችላል።

ይህ ክፍል ከዚህ የተሻሻለ የወተት ከብቶች እርባታ መመርያ ሌሎች ክፍሎች ጋር አብሮ የሚሰራጭ ለአነስተኛ ወተት ከብት እርባታ ጣቢያ ተብሎ በተዘጋጀ የመረጃ መመዝገቢያ ቅፆች ጋርተገናዝቦ የተዘጋጀ ሲሆን በጥምረት መጠቀም ተገቢ ነው። በሦስት ንዑሳን ክፍሎች ተከፍሎ ለወተት ከብት አርቢዎች ጠቃሚ የሆኑ የንግድ ስራ አመራር አያያዝ ይዞ ቀርቧል።



## 5.1 በወተት ከብቶች እርባታ ጣቢያ መዝገብ አያያዝ መመሪያ

**የወተት ከብቶች እርባታ ጣቢያ መረጃ ለርባታው እንደ ፊት መስታወት ማለት ነው። የእርባታውን የረጅምና የአጭር ጊዜ ጉዞውን (አዋጭነቱን) ፍንትው አድርጎ ያሳያል።**



ለወተት ከብቶች እርባታ ጣቢያ መረጃ አያያዝ እንዲያመች የእርባታው ከብቶች እንደ እድሜያቸው ለየብቻ ተለይተው መያዝ አለባችው። በዚህም መሰረት በሚከተሉት ሁኔታ ከብቶች መከፋፈል ተገቢ ነው፣

1ኛ. የወተት ላሞች

2ኛ. ጊደሮች (ከአንድ አመት በላይ የሆናቸውን)

3ኛ. ጥጆች (ከ3-12 ወራት)

4ኛ. ታዳጊ ጥጆች (ከ0-3 ወራት)

## 5.2 በወተት ከብቶች እርባታ ጣቢያ መረጃ መዝገብ አይነቶችና አጠቃቀም

**በሚከተለው ሁኔታ የተገለጡት 4 የመረጃ መሰብሰቢያ ቅፆች በአነስተኛ የወተት ከብት አርቢዎች በቀላሉ መሞላት እንዲችሉ ታስበው የተዘጋጁ ናቸው ፡፡ ከዚህ የኤክስቴንሽን ፅሑፍ ጋር አብረው የሚሰራጩ ናቸው፡፡**

### ቅፅ 1. የወተት ምርት መመዝገቢያ (በወር ሁለት ግዜ ብቻ የሚሞላ)

| የላም ስም (ቁጥር) | ላሟ የወለደችበት እለት (ቀን) (ወር) (ዓመት) | የወተት ምርት (ኪ.ግ) የወለደችበት እለት ወር______________አመት_____________ | | | | | | የወሩ ምርት (ኪ.ግ) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የወሩ የመጀመሪያ ሳምንት የአንድ ቀን ምርት | | | የወሩ 3ኛ ሳምንት የአንድ ቀን ምርት | | | |
| | | ጠዋት | ማታ | የቀን ምርት | ጠዋት | ማታ | የቀን ምርት | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |

*የወሩ ምርት =15 X (የቀን 1 ምርት+ የቀን 2 ምርት). የዚህ ቅፅ ሰንጠረዥ የሚወሰደው በዕረባታ ጣቢያው ባሉ ላሞች ብዛት ነው.

### ቅፅ 4. የወተት እርባታው የከብቶች ንብረት ቁጥር መመዝገቢያ

(በአመቱ መጨረሻ የሚሞላ)

| ዕለት (ቀን) (ወር) (ዓመት) | | | | |
|---|---|---|---|---|
| የከብቶች አይነት | የከብቶች ብዛት | የከብቶች ግምታዊ የገበያ ዋጋ (ብር) | የእርባታው ንብረት ዓይነት | የንብረቱ ግምታዊ የገበያ ዋጋ (ብር) |
| የወተት ላሞች | | | | |
| የነጠፉ ላሞች | | | | |
| ጊደሮች (>12 ወር) | | | | |
| ጥጆች (3-12 ወር) | | | | |
| ታዳጊ ሴት ጥጆች (0-3 ወር) | | | | |
| ታዳጊ ወንድ ጥጆች (0-3 ወር) | | | | |
| ኮርማዎች | | | | |

### ቅፅ 3. የወተት ከብት እርባታ ወጭና ገቢ መመዝገቢያ

| የከብት እርባታው ስም________________አመት __________ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| የወጪ ዕለት (ቀን) (ወር) (ዓመት) | የወጪው ዝርዝር | የወጪው መጠን (ብር) | የገቢው ቀን (ቀን) (ወር) (ዓመት) | የገቢው ዝርዝር | የገቢው መጠን (ብር) |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |

### ቅፅ 2. የእርባታ መከታተያ መዝገብ

| የእርባታው ስም _______________ ___________________ | እርባታው የተምሰረተበት ወርና አመት ____________ |
|---|---|
| የላሟ ስም / ቁጥር _______________ ___________________<br>ላሟ የወለደችበት እለት /ቀን/ ወር/ ዓመት / ______________ | የላሟ አባት ቁ/ስም ___________________<br>የላሟ እናት ቁ/ስም ___________________ |
| ላሟ ከውጭ የተገዛች ከሆነ ምንጭ __________________<br>ላሟ የተገዛችበት ብር ____________________ | ላሟ የተወገደችበት ዕለት __________________<br>ምክነያት ____________________<br>በሽያጭ ከሆነ ብር ___________________ |

| | | ጥጆች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1ኛ ጥጃ | 2ኛ ጥጃ | 3ኛ ጥጃ | 4ኛ ጥጃ | 5ኛ ጥጃ | 6ኛ ጥጃ |
| | 1ኛ | | | | | | |
| | 2ኛ | | | | | | |
| | 3ኛ | | | | | | |
| | 4ኛ | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | 1ኛ | | | | | | |
| | 2ኛ | | | | | | |
| | 3ኛ | | | | | | |
| | 4ኛ | | | | | | |
| ላሟ ለመውለድ የምትጠበቅበት እለት / ቀን/ ወር /ዓመት/ | | | | | | | |
| ላሟ የወለደችበት እለት /ቀን/ ወር / ዓመት/ | | | | | | | |
| ላሟ የነጠፈችበት እለት /ቀን/ ወር / ዓመት/ | | | | | | | |
| የላሟ የአለባ ቀን ብዛት | | | | | | | |
| የጥጃው ፆታ ስም/መለያ ቁጥር | | | | | | | |
| በ2 ጥጆች መሃል ያል ጊዜ | | | | | | | |
| የላሟ አጠቃላይ የወተት ምርት (ኪ.ግ) | | | | | | | |

## 5.3 የወተት ከብቶች እርባታ የንግድ ስራ አመራር

- ለወተት ከብቶች እርባታ ወጪ የመኖ ወጪ ትልቁን ድርሻ (እስከ 9/10ኛ) ይወስዳል። መኖ በራስ ማሳ ላይ በማምረት ወጪ መቀነስ ተገቢ ነው።
- በባለሙያ የተደገፈ ወጪ ቆጣቢ የመኖ ቀመር ማዘጋጀትና ላሞች በሚሰጡት የወተት መጠን መመገብ ከአላስፈላጊ የመኖ ወጭ ያድናል።
- ምርታማ ከሆኑ ላሞች የሚገኙትን ጥጆች በሚገባ ተንከባክቦ ቶሎ ቶሎ ላሞችን መተካት የወተት ገቢን ይጨምራል ። ምርታማ ያልሆኑ ላሞች ወጪያቸው ከፍ ያለ ስለሚሆን በምርታማዎቹ መተካት አለባቸው።
- የከብቶችን በሽታ በመከላከል፣ሞትን፣የህክምና ወጪን እና የምርት ማሽቆልቆልን በመቀነስ ትርፋማ መሆን ይቻላል።
- የላሞችን ስነ-ተዋልዶ በሚገባ መረጃ በመያዝ መከታተል ከተቻለ፣ ላሞች በአመት አንድ ጥጃ እና ከፍ ያለ የወተት ምርት መስጠታቸውን በማረጋገጥ ትርፋማ መሆን ይቻላል።



አነስተኛ የወተት ማቀነባበሪያ